ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ሰላምነ

ዘረሰዮሙ አሐደ ለክልዔሆሙ ፡ ኤፌ ም ፪ ቍ ፲፬

፲፰ኛ ዓመት ቍጥር ፪

አ ፡ አ ፡ መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ. ም.

# ተክለ፡ሃይማኖት።

ይህ ድርሰት ለሃይማኖትና ለምግባር ለጊዜውም ዜና መዋዕል መግለጫ የንባቡን ቀጥተኛ ትርጓሜ ከመከተል ጋር ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ መታሰቢያ ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ተሰየመ ።

| | | |
|---|---|---|
| የድርሰቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 1.20<br>» » አንዱ 0.5<br>ለውጭ አገር እጥፍ ይሆናል ። | በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክና ዜና ማደራጃ ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት ታተመ ። | በወር ሁለት ጊዜ ይወጣል ።<br>የፖስታ ሳጥን ቍጥር 12.83 |

## ጼዴንያ ።

ከመ| መልአኩ ፈለቀ ።

ጼዴንያ በምትባለው ሀገር በእመቤታችን ድንግል ማርያም ስም የተሠራች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ነበረች ፤ ይችውም ቤተ ክርስቲያን በብዙ ጌጣ ጌጥ የአማረችና የተዋበች ፤ ክፍ ያለች ቤተ ክርስቲያን ከመሆኗም በላይ ፤ በውስጧ ከ፬ ወንጌላውያን አንዱ ሉቃስ የሣላት የእመቤታችን ሥዕል ይገኝባት ነበር ።

ይችውም የእመቤታችን ሥዕል ብዙ ተአምራት ማድረጓን እየሰሙ ከሥዕሏ በረከት እናገኛለን በማለት ብዙ ሰዎች በዓመት በዓመት ወደ ጼዴንያ ሀገር ይሄዳሉ ።

አፍርንጊ በምትባለዋ ሀገር በብዙ ወርቅና ብር ፤ በብዙ ሶንቍ የከበረ አንድ ባለ ጸጋ ነጋዴ ነበር፤ይኸውም ሰው (ነጋዴ) የዚችን ሥዕል ዜና እየሰማ «ወዮ የእመቤቴን ሥዕል አግኝቼ፣ እጅ ነሥቼ፣ ከሥዕሏ በረከት ደርሶኝ» እያለ ይመኝ ነበር ።

ከዕለታት በአንድ ቀን ጼዴንያ ወደ ምትባለው ሀገር ሄዶ የእመቤታችን ሥዕል ካለችበት ቤተ ክርስቲያን ደረሰ። ከዚያም ብዙ ቀን ተቀምጦ ሳለ ፤ ይችን ሥዕል ስጡኝ ብሎ መነኰሳቱን ፤ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን ለመነ ፤ እነሱም አይሆንም አሉት ። ከዚህ በኋላ ይህ ነጋዴ ሥዕሏን ሰርቆ ወደ ሀገሩ ይወስድ ዘንድ አሰበ፤ ሥዕሊቱን አግኝቶ የሚወስድበትን ዘዴ እያጠናና ቤተ ክርስቲያኗንም እያገለገለ ሁለት ዓመት ተቀመጠ ። መነኰሳቱም አውቀውበት በሩን ያስጠብቁበት ነበር ። ሰርቆ ለመውሰድ እንዳልተቻለው ባወቀና በተረዳ ጊዜ ሾተል ይዞ ፤ እጁን በመስኮት አዝልቆ ከሥዕሏ የሥጋቍራጭ ያህል ቈረጠና ያዘ ፤ ወዲያው ወደ ሀገሩ ሊሄድ ተነሣ ። ያንጊዜ ከሥዕሏ ደም ወጣ ። መነኰሳቱም ለጸሎት በሚገቡበት ጊዜ አይተው ደነገጡ ፤ አዘኑ፣ወዲያው ያን ነጋዴ ቢያስፈልጉ አጡት ፤ እሱም ያችን የሥዕል ቍራጭ ይዞ ከከተማው በአንድ በኵል ተሠውሮ ስለነበር ፥ በፍጥነት ፈልገው አገኙት ፤ ይገድሉትም ዘንድ ወደዱ ። ያን ጊዜ «እኔን ስለመውደዱ ክብር ሊሆነው ወሰደ እንጂ ለክፋት አይደለምና አትግደሉት ፤ ተዉት »የሚል ቃል ከሥዕሊቱ ተነገረ ። ይህን የተቆረጠሙን ሥዕል ወስደው ቢያጣብቁት እንደነበረ ሁኗል ። ይህ የሆነበት መስከረም ፲ ቀን ነው ። ለዚህም ሰው ክብር ሆኖ ሲነገርለት ይኖራል ፤ ክብሩ አልቀረበትም ። የእኛም ቤተ ክርስቲያን ይህን ትልቅ ተአምር በመመልከት ፥ የእመቤታችን ሥዕል በጼዴንያ ሀገር የሠራችውን ተአምር ለማስታወስና ወደ ኢትዮጵያም የገባችበትን ቀን ለማክበር በመስከረም ፲ ቀን የጼዴንያ በዓል ብላ ታከብረዋለች ፤ ታስከብረዋለች። ከእመቤታችን በረከት እንዲያድለን ልዑል እግዚአብሔርን እንለምነው ።

## እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በደህና አሸጋገረዎ ።

መስከረም ፪ ቀን ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ብፁዕ ወቅዱስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ አቡነ ባስልዮስ እንኳን ከዘመነ ሉቃስ ወደ ዘመነ ዮሐንስ በሰላም አሸጋገረዎ ለማለት የቀረቡትን የጠቅላይ ቤተ ክህነት ከፍተኞች ባለ ሥልጣኖችንና ሹማምንትን ፤ እንዲሁም የየክፍሉ ሠራተኞችን፤ ክቡራን የደብር አለቆችንና ሊቃውንትን በመንበረ ክናቸው ተቀብለው እጅ አስነሥተዋቸዋል ።

የድርሰትና ስብከት ክፍል ሠራተኞችም በክፍሉ ኃላፊ በክቡር መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ አቅራቢነት እጅ ከነሡ በኋላ ፥ ክቡር መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ በክፍሉ ሠራተኞች ስም ሁነው የቅዱስነታቸውን ሙሉ ጤንነትና ረጅም ዕድሜ የሚመኝ ፤ እንዲሁም በስብከትና ድርሰት ክፍል የተሻሻለውን የሥራ ርምጃ የሚገልጽ አጭር ንግግር አደረጉ ። ቅዱስነታቸውም መልስ ሲሰጡ ባለፈው የሥራ ክንውን ካመሰገኑ በኋላ ለወደፊቱም በርቱ ጀምሮ ከመተው ያድናችሁ በማለት የሚያበረታታ አባታዊ ምክር ሰጥተዋል ።

## ትርጉሙ ይገለጽልን ።

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ።

ባለፈው በበዓለ ፍልሰታ ሰሞን አዘውትሬ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የሚዘመሩትን መዝሙሮች ለመስማት ቅዳሴም ለማስቀደስ እድል ገጥሞኝ ነበር ።

በቅዳሴው ሰዓት የሚዘመሩትን መዝሙሮች ሳዳምጣቸው ልብንና አእምሮን ከክፉት ጐዳና አስፈንጥረው ወደ ደግ መንገድ ይመራሉ ፤ ልብም ሙሉ ጸጥታን ካገኘ እንደ ቀሳውስቱ ዘምሩኝ ፤ ስለ እኔ በጥሩ ድምጽና ዜማ ተናገሩልኝ የሚል ስሜትን ይሰጣል ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ዋና ችግሩ ምን ይመስላችኋል ? እንደምታውቁት በአዲሱ ዘመን የተገኙ ፥ እንዲሁም የሚገኙ ወጣቶች እድሜአቸው ሰባት ወይም ስምንት ሲሆን ከጥንት ተያይዞ በመጣው በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ገብተው ፊደልን ፤ መልእክተ ሐዋርያን፣ ወንጌልን፤ ዳዊትን ለአጭር ጊዜ በግዕዝ ቋንቋ

www.ethiopianorthodox.org

